# ዓለም አቀፋዊው የአናባፕቲስቶች የጋራ እምነት

Mennonite World Conference
A Community of Anabaptist related Churches

Congreso Mundial Menonita
Una Comunidad de Iglesias Anabautistas

Conférence Mennonite Mondiale
Une Communauté d'Eglises Anabaptistes

**በእግዚአብሔር ጸጋ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘውን መልካሙን የዕርቅ ዜና ልንኖረውና ልናውጀው እንሻለን። ሁልጊዜ እና በሁሉም ቦታ የአንዱ የክርስቶስ አካል እንደመሆናችን፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መግለጫዎች የእምነታችን እና የልምዳችን ማዕከል አድርገን እንቀበላለን፤**

1 እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ፣ እና መንፈስ ቅዱስ ሆኖ፣ በኀጢአት የወደቀውን ሰው ለማዳን የሚፈልግ ፈጣሪ በመሆን ተገልጦአል፤ ይህም አንድን ሕዝብ በኅብረት፣ በአምልኮ፣ በአገልግሎትና፣ በምስክርነት ታማኝ እንዲሆን ጥሪን በማቅረብ ነው።

2 ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። እርሱ በሕይወቱ፣ በትምህርቶቹ፣ በመስቀሉ እና በትንሣኤው፥ እንዴት ታማኝ ደቀ መዛሙርት መሆን እንደምንችል አሳይቶናል፤ ዓለምን ተቤዥቷል፤ ደግሞም የዘላላም ሕይወትን ሰጥቶናል።

3 እንደ ቤተ ክርስቲያን ከኀጢአት እንድንመለስ፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት እውቅና እንድንሰጥ፣ እምነታችንን በማወጅ ጥምቀትን እንድንቀበል እና ክርስቶስን በሕይወታችን እንድንከተል የእግዚአብሔር መንፈስ የጠራን ማኅበረሰብ ነን።

4 እንደ አንድ እምነት ማኅበረሰብ፥ መጽሐፍ ቅዱስን የእምነታችን እና የሕይወታችን ባለሥልጣን እንደሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በጋራ በመተርጎም እና በኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለይቶ በማወቅ መታዘዝን እንዳለብን እናምናለን።

5 የኢየሱስ መንፈስ በሕይወታችን አቅጣጫ ሁሉ በእግዚአብሔር እንድንታመን ኀይል ይሰጠናል፣ በዚህ ምክንያት አመጽን የካድን፣ ጠላቶቻችንን የምንወድድ፣ ፍትሕን የምንሻ፣ ያለንን ሀብት ለሚያስፈልጋቸው የምናካፍል፣ የሰላም ሰዎች እንሆናለን።

6 የጋራ በሆነ የተጠያቂነት መንፈስ ለአምልኮ፣ የጌታን እራት ለመካፈል እና የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት በቋሚነት እንሰበሰባለን።

7 በዓለም ዙሪያ እንዳለ የእምነት እና የሕይወት ማኅበረሰብ፥ የብሔር፣ የዘር፣ የመደብ፣ የፆታ፣ የቋንቋ ወሰንን ሁሉ  እናልፋለን። ከክፉ ኀይላት ጋራ ሳንስማማ፣ ሌሎችን እያገለገልን የእግዚአብሔር ጸጋ ምስክሮች ሆነን፣ ፍጥረትን በመንከባከብ እና ሰዎች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝ እና ጌታ አድርገው እንዲያውቁት በመጋበዝ በዓለም ውስጥ ለመኖር እንሻለን።

**በእነዚህ የእምነት አንቀጾች፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ ከልባቸው ቁርጠኛ ደቀ መዝሙር መሆንን ካመለከቱን፣ የ16ኛው ክፍለ ዘመን ቀደምት አናባፕቲስት አባቶች መነቃቃትን እናገኛለን፡ ፡ የክርስቶስን ዳግም መምጣት እና የእግዚአብሔርን መንግሥት ፍጻሜ በልበ ሙሉነት ስንጠባበቅ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በኢየሱስ ስም ለመኖር እንተጋለን።**



ከሜኖናይት ዓለማቀፍ ጉባኤ ስብሰባ የተወሰደ      ጠቅላላ ጉባኤ      መጋቢት 15፣ 2006